# ቃልማ ህያው ነው!

ከዓሣዬ

11/08/10

ጊዜው ተለዋውጦ፣ዘመኑ ተሸሮ
ቃል በራዥ ልክስክስ፣በጥቅም ታውሮ
ትግሉን ለማዳከም፣በቃል ላይ አመንዝሮ፣
ዓየን እጁን ሲሰጥ፣ለዘረኞች አድሮ ።

ቃል መንምኖ ቢታይ፣ነጭ ዓምላኪው በዝቶ
ወገቡን ሲጠረዝ፣በጥቅም ድሪቶ
ቃልማ ህያው ነው፣መቼ እጁን ሰጥቶ
ኮርቶ ይቆማል እንጂ፣በሕዝቡ ተማምኖ፣በዕምነቱ ጸንቶ
ግንባሩን ሣያጥፍ፣በትግል ድል ነስቶ! ።

ከዓለም አቀፍ ጠላት፣ከአገር በቀል ባንዳ
ቃሉን እንዴም ሣያጥፍ፣ህዝቡንም ሣይከዳ፣
ሥልጣን ለሕዝብ ብሎ፣ቃሉን ባከበረ
በዓላማው ጸንቶ፣ትግሉንም ቀጥሎ፣በቃሉ ባደረ
አረጀ ይሉታል፣ዓርባ ዓመት አሥቆጠረ፣
ቃሉን አላጥፍ ብሎ፣በሥልጣን ድለላ፣ሥላልተበገረ
ውድ ሕይወቱን ከፍሎ፣ሃገሩን ሊታደግ ቃል ሥላከበረ ።

ቃልማ ሃይል ነው፣አጥብቆ ለያዘው
ለዜግነት ኩራት፣ለአገር ወዳድነት፣መለኪያው እንጂ ነው፣
ቃልማ አይሞትም፣ውድ ሕይወቱን ሰጥቶ ለሚንከባከበው
ምን ትግሉ ቢራዘም፣ምሬቱ አይበግረው!
ከመሃል አይቆምም፣አንዴ የገባውን ቃል፣ከዳር ሣያደርሰው
እንደ እንቶኔው መንደር፣
ጅብ እንዳየች በቅሎ፣ቃል ባዕዱ ሁኖ እንደሚደነብረው ።

በሰባራ ወገብ፣በአልጠግብ ባይነት፣እየተልከሰከሰ
በሆይ ሆይታ ጎራ፣
ለዘረኞች መንጋ፣በአሥር ጣት ፈርሞ እየተጎነበሰ
በፈሪ ለናቱ፣በባዶ ተሥፈኞች፣ቃል ግን እረከሰ፣

ታድያ እኮ፣
ከጭቁን ሕዝብ ጋር፣እጅና ጓንት ሁኖ
ቃልማ ህያው ነው፣መቼ እጁን ሰጥቶ
ኮርቶ ይቆማል እንጂ፣በዕምነቱ ጸንቶ
ለአንዴና ለሁሌም፣ፋሺስት ዘረኛነው ድባቅ አስገብቶ
ቆርጦ በመታገል፣ድልን ተቀዳጅቶ
በቃሉ እንደጸና፣ሶሻል ዴሞክራሲን፣በሃገሩ መሥርቶ! ።

This document was created with Win2PDF available at http://www.win2pdf.com.
The unregistered version of Win2PDF is for evaluation or non-commercial use only.
This page will not be added after purchasing Win2PDF.